# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰበር መ/ቁ/217639

ሐምሌ 28 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡ ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡አቶ ተስፋሚካኤል ገብረጻዲቃን

ተጠሪ፡ሙሉ አብርሃ ኮንስትራክሽን መሳሪያዎች አከራይ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

መዝገቡ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል በተደረገዉ የተሽከርካሪ ኪራይ ዉል መሰረት ለተከፈለዉ ገንዘብ አመልካች ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ አለበት ተብሎ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠዉ ዉሳኔ በይግባኝ ሰሚ ችሎት መጽናቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በሚል ዉሳኔዉ እንዲታረም አመልካች በቀን 06/04/2014ዓ.ም ጽፎ ባቀረበዉ አቤቱታ መነሻ ነዉ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ሲታይ ክርክሩ በተጀመረበት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ፤አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ተጠሪ ባቀረበዉ ክስ ባለን የመኪና ኪራይ ዉል ግንኙነት ለአመልካች ከከፈልኩት ገንዘብ ዉስጥ ብር 704,702.03 የግብይት ደረሰኝ እንዲሰጠኝ ወይም እንደገቢ ተይዞ የከፈልኩትን የተጨማሪ እሴት ታክስ እና ፍሬ

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ግብር ብር306,174.80 ክሱ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ተከፍሎ አለቀ ድረስ ከሚታሰብ ወለድ 9% ጋር እንዲከፍለኝ እንዲወሰን በማለት ዳኝነት የጠየቀ ሲሆን አመልካች በበኩሉ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሊሆን እንደሚገባ፤በፍሬ ነገር ረገድ ተጠሪ በዉሉ መሰረት በጊዜ ሰነዶችን አቅርቦ ገንዘብ ባለመክፈሉ በፍርድ ሃይል ተገዶ ስለከፈል ግዴታዉን ሳይወጣ አመልካች ደረሰኝ እንዲሰጥ ለመጠየቅ መብት የለዉም በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የዳኝነት ስልጣን የተመለከተዉ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በብይን ዉድቅ በማድረግ በፍሬነገር ረገድ የቀረበዉን ክርክር መርምሮ በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 19(3) መሰረት አመልካች ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ አለበት በማለት በክሱ መሰረት ደረሰኝ እንዲሰጥ ወይም በአማራጭ የተጠየቀዉን ገንዘብ እንዲከፍል ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡አመልካች ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበዉ ይግባኝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሰረት ተሰርዟል፡፡

ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረበዉ በዚህ ላይ ሲሆን ይዘቱም ባጭሩ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል በተደረገዉ የመኪና ኪራይ ዉል ከ 01/03/2007ዓ.ም እስከ 03/13/2007ዓ.ም በነበረዉ ቆይታ ጊዜ መኪኖቹ ላስገኙት ገቢ በአዋጅ ቁጥር 979/2008 አንቀጽ 33(4) እና አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 17(2) እና 28(2) መሰረት መካከለኛ ግብር ከፋይ ሰነድ የመያዝ እና ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ ገቢዉ ከተገኘበት ቀጥሎ ባሉት 5ዓመታት ብቻ በመሆኑ ተጠሪ ገቢዉ ከተገኘ ከ5ዓመት በኋላ ያቀረበዉ ደረሰኝ ጥያቄ ክስ በይርጋ ሊታገድ ሲገባ መታለፉ እና ተጠሪ በንግድ ስያሜ ክስ መመስረቱ የስነስርዓት ህግ የጣሰ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለሆነ እንዲታረም በማለት አመልክተዋል፡፡

የአመልካች አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ የስር ፍርድ ቤት አግባብነት ያለዉ ህግ የንግድ ህግ ነዉ በማለት 10ዓመት ይርጋ አላለፈበትም ማለቱ የታክስ አስተዳደር እና የገቢ ግብር አዋጅ ድንጋጌዎችን ያገናዘበ መሆን አለመሆኑን እና አመልካች ደረሰኝ እንዲሰጥ ወይም ገንዘቡን እንዲከፍል የተወሰነበት አግባብ በግራ ቀኙ መካከል ከተደረገዉ ዉል አንጻር እንደዚሁም ሌሎች ነጥቦች ለመመርመር በሚል ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ አዟል፡፡

የተጠሪ ጠበቃ በቀን 28/06/2014ዓ.ም ጽፎ ባቀረበዉ መልስ የአመልካች እና የተጠሪ ግንኙነት የዉል ግንኙነት ስለመሆኑና ለጉዳዩ አግባብነት ያለዉ ይርጋ ጊዜ ፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1845 መሰረት 10ዓመት መሆኑን፤የታክስ አስተዳደር አዋጅ ሆነ የገቢ ግብር አዋጅ ድንጋጌዎች ላይ

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የተገለጸዉ ጊዜ ገደብ የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ ያለበት ሰዉ ሰነድ ይዞ የሚያቆይበት ጊዜ የሚመለከት እንጂ ደረሰኝ መቁረጥ ግዴታ የሚመለከት አለመሆኑን እንዲሁም ይርጋ ጊዜዉ ሊታሰብ የሚገባዉ ክፍያዉ በሂሳብ አጣሪ ተጣርቶ ሰበር ችሎት በመ/ቁ/ 186610 ላይ የመጨረሻ ዉሳኔ ከተሰጠበት መስከረም 25 ቀን 2013ዓ.ም ጀምሮ ነዉ በማለት ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራቀኙ ክርክር አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከትነው ሲሆን ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ከተባለበት ጭብጥ አንጻር የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡መዝገቡን መርምረን እንደተገነዘብነዉ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የተደረገ የመኪና ኪራይ ዉል ነዉ፡፡ዉል መኖሩ በግራቀኙ የታመነ ጉዳይ ነዉ፡፡አከራካሪዉ ጉዳይ በዉሉ መሰረት ለተፈጸሙት ክፍያዎች ደረሰኝ ያልቆረጠበት ክፍያ በመኖሩ ነዉ፡፡ከዚህ ጋር በተያያዘ ቀሪ ገንዘብ ለማስከፈል ተጠሪ ባቀረበዉ ክስ ላይ ከስር ፍርድ ቤት ጀምሮ እስከዚህ ሰበር ችሎት ድረስ ክርክር ተደርጎ በልዩነት የተገኘ ቀሪ ገንዘብ ተጠሪ ለአመልካች እንዲከፍል ሰበር ችሎት በመ/ቁ/186610 ላይ መስከረም 25 ቀን 2013ዓ.ም ዉሳኔ መሰጠቱን ክርክሩ ያሣያል፡፡ይህንኑ ተከትሎ ተጠሪም በበኩሉ ደረሰኝ ያልተቆረጠበት ክፍያ አለ በሚል ደረሰኝ እንዲቆረጥለት ባቀረበዉ ክስ ላይ አመልካች የሚከራከረዉ ክሱ የቀረበዉ ዉሉ ከተፈጸመ ከ5ዓመት በኋላ በመሆኑ ይርጋ ጊዜ አልፎበታል በማለት ነዉ፡፡በአጣሪ ችሎት የተያዘዉ ጭብጥ ይርጋ መቃወሚያ ዉድቅ የተደረገበትን አግባብነት ለመመርመር ነዉ፡፡ይርጋ ደንብ መብት ለማስከበር የሚቀርብ ክስ */limitation of action/* ቀሪ የማድረግ ዉጤት ያለዉ የህግ ጽንሰ ሃሳብ ነዉ፡፡የይርጋ ደንብ */period of limitation/* ዓይነተኛ ዓላማ አንድ ግዴታ እንዲፈጸምለት የሚጠይቅ ባለመብት በህጉ በተገለጸ የጊዜ ገደብ ዉስጥ በመብቱ ባለመስራቱ የመብት ጥያቄዉ በጊዜ ማለፍ ምክንያት ቀሪ የሚሆንበት በሌላ በኩል ግዴታ ያለበትን ወገን ግዴታዉን እንዲፈጽም ከሚቀርብበት ክስ ነጻ የማድረግ ዉጤት ያለዉ ነዉ፡፡የይርጋ ጊዜ እርዝማኔ እንደጉዳዩ ዓይነትና ባሕርይ የሚለያይ ስለመሆኑ የይርጋ ደንብ የሚመለከቱ ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ስለዚህም ተፈጻሚነት ያለዉ ይርጋ ጊዜ ለመለየት የሚቻለዉ የተጠየቀዉ ዳኝነት ዓይነት ወይም የክስ ምክንያት እና በመብቱ መስራት የሚቻልበትን ጊዜ በሚመለከት ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለዉን ህግ መሰረት በማድረግ መሆን አለበት፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ ክሱ መነሻ ያደረገዉ የዉል ግንኙነትን ነዉ፡፡በመሰረቱ የፍትሓብሔር ሃላፊነት የሚመነጨዉ ከዉል ወይም ከህግ ሊሆን ይችላል፡፡ከዉል የሚመነጭ ሃላፊነት አለ የሚባለዉ ስለዉል አመሰራረት የሚደነግገዉ የፍትሓብሔር ህግ ድንጋጌዎች ላይ የተመለከቱ

*ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

መስፈርቶችን አሟልቶ በተቋቋመ ዉል የተፈጠረ መብትና ግዴታ ሲኖር ነዉ፡፡ስለዉሎች አመሰራረትና አፈጻጸም የሚደነግገዉ የፍትሓብሔር ህግ እንደሚያስገነዝበን ዉሉ በተዋዋይ ወገኖች ላይ መብትና ግዴታ ሊፈጥር የሚችለዉና ህጋዊ አስገዳጅነት የሚኖረዉ በህጉ የተመለከቱትን መሰረታዊ ጉዳዮችን/essenetial elements of contract/ አሟልቶ ሲገኝ ነዉ፡፡ይኸዉም ተዋዋይ ወገኖች ዉል ለማድረግ ችሎታ ያላቸዉ መሆን፣በተዋዋዮች ነጻ ፈቃድ የተደረገ መሆኑ፣የዉሉ ጉዳይ የሚቻልና በግልጽ የሚታወቅ እና በህግ ያልተከለከለ መሆኑ እና ህጉ ሲጠይቅ የዉሉ አጻጻፍ ስርዓት ወይም ፎርም የተሟላ መሆኑን የሚመለከቱ ናቸዉ፡፡(የፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 1678 እና 1731/1/ ይመለከቷል)፡፡

ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የተደረገ የመኪና ኪራይ ዉል ግራቀኙ የተማመኑበት ጉዳይ ነዉ፡፡ዉልን መሰረት አድረጎ የሚቀርብ ክስ ህግ በሌላ አኳኋን ካልወሰነ በቀር ዉሉ እንዲፈጸም ወይም ካለመፈጸሙ የተነሳ ስለሚደርስ ጉዳት ወይም ዉሉ እንዲፈርስ የመጠየቅ መብት በአስር ዓመት ይርጋ ቀሪ እንደሚሆን የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1845 በግልጽ ደንግጓል፡፡የተጠሪ ዳኝነት ጥያቄ ዉልን መሰረት ያደረገ በመሆኑ ክስ የማቅረብ መብቱ በይርጋ የታገደ መሆን አለመሆኑ ከዚሁ የ10ዓመት ይርጋ ጊዜ ገደብ አንጻር መታየት አለበት፡፡አመልካች የሚከራከረዉ ተጠሪ ክስ ያቀረበዉ ከ5ዓመት በኋላ ነዉ በማለት እንጂ 10ዓመት ጊዜ አልፎበታል በማለት አይደለም፡፡አመልካች ለክርክሩ መሰረት ያደረገዉ የታክስ አስተዳደር አዋጅ እና የገቢ ግብር አዋጅ ድንጋጌዎች ላይ የተመለከተዉን ጊዜ ገደብ መሰረት በማድረግ መሆኑን ከላይ ተመልክተናል፡፡

የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 ም ሆነ የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 የሚደነግጉት እንደቅም ተከተሉ ስለታክስ አስተዳደር እንዲሁም ግብር እና/ወይም ታክስ ሰብሳቢ ተቋማት ስልጣንና ሃላፊነት እና ተያያዥ ጉዳዮችን በሚመለከት ነዉ፡፡ከዚህም በተጨማሪ ታክስ ወይም ግብር ከፋይ የሆነ ሰዉ ያለዉን መብትና ግዴታ የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን ያካተተ ነዉ፡፡በሌላ አገላለጽ እነዚህ ህጎች ተፈጻሚነታቸዉ በታክስ ሰብሳቢዉ መ/ቤት እና በታክስ ከፋዩ መካከል የሚኖረዉ ግንኙነት ላይ ነዉ፡፡በተያዘዉ ክርክር አመልካች ክርክሩን ለማስረዳት የጠቀሳቸዉ የአዋጆቹ ድንጋጌዎች ይዘት ሲታይ የሂሳብ ሰነድ የመያዝ ግዴታ ያለበት ታክስ ከፋይ ሰነዶችን ይዞ የማቆየት ጊዜ ገደብ በሚመለከት እንደነገሩ ሁኔታ 5ዓመት ወይም በንግድ ህጉ የተመለከተዉ ከፍተኛ ጊዜ ገደብ አስር ዓመት መሆኑን የሚያመለክት እንጂ በሰዎች መካከል በዉል ላይ የተመሰረተ ግንኙነት ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ይርጋ ደንብ ስለመሆኑ አልተመላከተም፡፡(በቅደም ተከተል አዋጅ ቁጥር 983/2008 እና አዋጅ

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ቁጥር 979/2008 አንቀጽ17(2) እና 33(4) ይመለከታል)፡፡ስለሆነም በአመልካች እና በተጠሪ መካከል በዉል ላይ ለተመሰረተ ግንኙነት የመነጨ የመብት ጥያቄ ተፈጻሚነት ያለዉ ይርጋ ጊዜ ስለዉሎች የተደነገገዉ የፍ/ብ/ህግ ድንጋጌ ቁጥር 1845 ላይ የተመለከተዉ አስር ዓመት ጊዜ ገደብ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

ሲጠቃለል ተጠሪ ለክሱ ምክንያት ያደረገዉ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የተደረገ የመኪና ኪራይ  ዉል መሆኑ አከራካሪ ባልሆነበት ሁኔታ አመልካች የታክስ አስተዳደር ህግ መሰረት በማድረግ ያቀረበዉ ይርጋ መቃወሚያም ሆነ የስር ፍርድ ቤት የንግድ ህግ ድንጋጌዎች ምርኩዝ አድርጎ የሰጠዉ ብይን ለተያዘዉ ክርክር አግባብነት የለዉም፡፡ ይሁንና የስር ፍርድ ቤት ክሱ አስር ዓመት አላለፈበትም በማለት የአመልካችን መቃወሚያ ዉድቅ ማድረጉ የዉል ግንኙነት ከፍተኛዉ ይርጋ ጊዜ አስር ዓመት ነዉ ከሚለዉ የፍ/ብ/ህጉ ድንጋጌ የሚጣጣም በመሆኑ ከዉጤት አንጻር ሲታይ መሰረታዊ ልዩነት የሚያስከትል አይደለም፡፡ስለሆነም የስር ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ ላይ በምክንያት ብንለይም በዉጤቱ በመስማማት ተጠሪ ደረሰኝ እንዲሰጠዉ ያቀረበዉ ክስ አስር ዓመት ይርጋ ጊዜ አላለፈበትም ተብሎ የተሰጠዉ ብይንም ሆነ አመልካች ደረሰኝ ለተጠሪ እንዲሰጥ ወይም በአማራጭ የተጠየቀዉን ገንዘብ እንዲከፍል ተብሎ የተሰጠዉ ፍርድ  ፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ2(4) እና 10(1/ሀ)አንጻር ሲታይ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ የሚባልበት ምክንያት አልተገኘም፡፡በዚሁ አግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ዉሳኔ

1ኛ/የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ በማጽናት በመ/ቁ/170792 ላይ በቀን 23/11/2013ዓ.ም የሰጠዉ ፍርድ ጸንቷል፡፡

2ኛ/በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ጋ

ማ ሳታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም